# በኢትዮጵያ የፍትህ ዘርፍ የሚፈፀሙ የሙስናና ብልሹ አሰራር ችግሮች፣ መንስኤና የመፍትሄ ሀሳቦች

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች:-**

መካሻ አበራ

ቴዎድሮስ ዳዊት

ጋሻዬ መረሳ

ቤዛዊት አስፋው

አብርሃም ሙሉጌታ

ኃ/ገብርኤል ጌዲኾ

ህሊና ጥላሁን

ማህሌት ሸዋንግዛው

የትናየት ደሳለኝ

9.1.በዚህ ጥናት ምእራፍ አምስት የሙስናና ብልሹ አሰራር ችግሮች ተብለው በዝርዝር የተመለከቱትችግሮች በተቋማትና በፌዴራልና በክልሎች ተለያይተው ተመልክተዋል፡፡ የእነዚህ ችግሮች ማጋጠም ተደጋጋሚነትን በተመለከተ ከመቶኛ አንጻር ያገኙት ውጤትም በሰነዱ ተመልክቷል፡፡ ይህ ጥናት የትኛዎቹ ችግሮች የሚበዛውን የፍትህ አካላት ተገልጋይና ባለድርሻ አካላት እንደሚስማማባቸው በመቶኛ አሳይቷል፡፡ ስለሆነም በንጽጽር ከፍተኛ የሆኑ መላሾች ችግሮች አሉባቸው የተባሉትን የአሰራር ችግሮች የሚመለከታቸው ተቋማት ከመላሾች ከተሰጠው ምላሽ አንጻር ቅደምተከተል በማውጣት የችግሮቹን መንስኤ በጥናት በመለየት የአሰራር ችግሮቹን ማስወገድ የሚችሉ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ስርአትን በመዘርጋት የተገልጋይና ባለድርሻ አካላቶች እርካታ እንዲጨምር እንዲያደርጉ አጥኚዎችይመክራሉ፡፡ በተለይም የፌዴራልም ሆነ የክልል ጸረ ሙስና ኮሚሽኖች የፍትህ አካላት የሰው ሀይል አስተዳደር (ባለሙያዎችንና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ጨምሮ) ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት እንዲሆን ከማድረግ አንጻር ቅድሚያ ሰጥተው ጥናት እንዲያደርጉበት በዚህ ጥናት ይመከራል፡፡

9.2.እንደ አጥኚዎች እምነት በዚህ ጥናት የሙስናና ብልሹ አሰራር አመላካች ተብለው የተዘረዘሩበት መስፈርቶች ወይም መለኪያዎች በቀጣይነትም የፍትህ ስርአቱ የአገልግሎት አሰጣጥ ከሙስና የጸዳ ለመሆኑ መለኪያ መስፈርቶች በመሆንም ያገለግላሉ፡፡ ተቋማቶች እነዚህን መስፈርቶች ወይም መለኪያዎች እንደሁኔታውም ከተቋማቸው ሁኔታና ከአዳዲስ ለውጦች አንጻር እያሻሻሉ በተወሰነ ጊዜ የተጋላጭነታቸውን ሁኔታ በመመዘን ችግሮችን ለማወቅና መፍትሄዎችን ለማቅረብ እንደሚጠቅሙዋቸው በማሰብ እንዲጠቀሙባቸው ይመከራል፡፡

9.3.በጥናቱ እንደተለየው ለፍትህ አካላት ጉቦ ወይም የማይገባ ስጦታ ወይም ክፍያ በማቅረብ ከፍተኛውን ደረጃ ይዞ የሚገኘው ራሱ ተገልጋዩ ህብረተሰብ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ በአጥኚዎች እምነት ለዚህ አንዱና

ዋናው ምክንያት ተገልጋዩ በፍትህ ዘርፉ ላይ ያለው የተዛባና የተሳሳተ አመለካከት ማለትም ጉቦ ካልሰጠሁ ፍትህ አላገኝም የሚል አመለካከት እንደሆነ ይገመታል፡፡ የፍትህ አካላት ከሙስና የጸዱ ቢሆንም፣ ተገልጋዩ ህብረተሰብ የፍትህ አካላት ከሙስና የጸዱ አይደሉም ብሎ የሚያምን መሆኑ በራሱ የፍትህ አካላትን ወደሙስናና ብልሹ አሰራር እንዲገቡ የሚገፋፋ በመሆኑ፣ የፍትህ አካላት በዜጎችና በህብረተሰቡ እንዲህ አይነት የተዛባ አመለካከት እንዳይኖር አሳታፊ መድረከቻቸውን፣ የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም እንዲህ አይነት የተዛቡ አመለካከቶች እንዲፈጠሩ መንስኤዎቹ ምን እንደሆኑ በመለየት የተለያዩ ዘዴዎችና ስልቶችን በመጠቀም እነዚህ የተዛቡ አመለካከቶች እንዳይኖሩ ወይም እንዳይፈጠሩ ሳይሰለቹ ተግተው መስራት ይኖርባቸዋል፡፡

9.4.ለሙስናና ብልሹ አሰራር የሚያነሳሱትን መንስኤዎች በተመለከተ ከራሱ ከተገልጋዩ አነሳሽነት በተጨማሪ ለሙስናና ብልሹ አሰራር መንስኤ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው ከተለዩት በአንደኛ ደረጃ የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስነምግባር ችግር ሲሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ የደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ማነስ እንደሆነ በጥናቱ የተሰባሰበው መረጃ አመልክቷል፡፡ እነዚህ ሁለቱ እርስ በርስ የሚመጋገቡ ናቸው፡፡ በዘርፉ ውስጥ የሚሰራው ባለሙያ የሙያ ስነምግባሩን አክብሮ የሚሰራ ቢሆንም፣ ይሁንና ደመወዙና ጥቅማጥቅሙ የማይበቃውና ለቤተሰቡም ለመኖር የማያስችለው ከሆነ፣ ወደሙስና ተግባር ከመግባት ይልቅ ስራውን መልቀቅን ይመርጣል፡፡ ይህም ዘርፉ መልካም ስነምግባር ያላቸውን ሰዎች እንዲያጣ ያደርገዋል፡፡ ይህ ማለት የደመወዝና ጥቅማ ጥቅም መሻሻል ሙስናን ያጠፋል ማለት አይደለም፡፡ የስነምግባር ችግር ያለበት ባለሙያ ደመወዙና ጥቅማጥቅሙ ከፍተኛ ቢሆንም ወደሙስና ተግባር ከመግባት አይመለስም፡፡ ይሁንና የደመወዙና ጥቅማ ጥቅሙ ማነስ መልካም ስነምግባር ያለው ወደዘርፉ እንዳይመጣ ማድረጉ ወይም በዘርፉ ውስጥ ያለው ስራውን እንዲለቅ ማድረጉ ግን እንደአጥኚዎች እምነት እውነት ነው፡፡ የስነምግባር ችግር ያለበት ሰው ግን ደመወዙና ጥቅማ ጥቅሙ አነስተኛ ቢሆንም፣ ህገወጥ በሆነ መልኩ አካክሰዋለሁ

ስለሚል የፍትህ ዘርፉ በባህርይው ለሙስናና የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ካለው ተጋላጭነት የተነሳ መልካም ስነምግባር የሌለውን የሚስብ መሆኑ አይቀርም። ስለሆነም እነዚህን ሁለት ችግሮች በጥምር መፍታት ያስፈልጋል። መልካም ስነምግባር ያለውን ባለሙያ ለማግኘት ወይም በስራው ላይ ለማቆየት ደመወዝና ጥቅማጥቅሙ ቢያንስ በበቂ ሁኔታ ሊያኖረው የሚችል (በተለይም የመኖሪያ ቦታና የትራንስፖርት ችግሮቹን የሚፈቱ ስልቶችን በመቀየስና ተግባራዊ በማድረግ) ና ስራውን ለመልቀቅ እንዳይፈልግ የሚያደርገው መሆን ይኖርበታል። በሌላ በኩል ወደዘርፉ የሚቀላቀሉት አዲስ ባለሙያዎች በእውነትና በሀቅ እንጂ በመደለያ፣ በዘመድ፣ አለቃን ወይም ሀላፊን ለማስደሰት የማይሰሩ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የስነምግባር ጥናቶችን በማካሄድ፣ ለሕገመንግስቱ ታማኝ ነኝ ብለው እራሳቸውን ታማኝ አስመስለው በማቅረባቸው ሳይሆን፣ ከቃላቸው ይልቅ በድርጊታቸው በመመዘን፣ እንዲሁም በስራ ላይ በሚገኙበት ጊዜ እንደነዚህ አይነት ኢስነምግባራዊ ባህርይ እንዳያሳዩ ተከታታይነት ያለው የስነምግባር ስልጠናና ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ፣ የስነምግባር ጥሰት ፈጽመው ሲገኙም የማያዳግም እርምጃ በመውሰድ መልካም ስነምግባር ያላቸው ብቻ የሚበረታቱበት ስርአትን መዘርጋት ያስፈልጋል።

9.5. ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመዋጋት በመፍትሄነት ከሚቀመጡት ጉዳዮች መካከል የፍትህ አካላት የሚሰሩባቸውን ግልጽ አሰራሮች በመመሪያ መደንገግ ነው። ከዚህ አንጻር የቅጣት አወሳሰን መመሪያ በምሳሌነት ሊጠቀስ ይችላል። በተመሳሳይ መልኩ (1) የካሳ አወሳሰን፣ (2) ዋስትና ሲሰጥ በዋስትና ሊጠየቅ ስለሚገባው የገንዘብ መጠን፣ (3) የማስረጃዎች ምዘናን በሚመለከት እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮችን በሚመለከት ዝርዝር መመሪያዎች በማዘጋጀት በፍትህ አካላት ግልጽነትን፣ የውሳኔ ተገማችነትን ለማሻሻል እንደሚረዳ ይመከራል።

በማጠቃለያው ዜጎች ህግን አክብረው የሚንቀሳቀሱት ሌሎችም ህጉን አክብረው ይሰራሉ ወይ? የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ህግን አክብረው ያለአድልዎ ይሰራሉ ወይ? ለሚለው ጥያቄያቸው አዎንታዊ ምላሽ ካላቸው ነው።

ዜጎች ህጉ አይከበርም ይጣሳል፣ ዳኞች፣ ፖሊሶች አድልዎ ይሰራሉ፣ በሙስና ይሰራሉ የሚል እምነት ካላቸው በእነሱ በኩልም ህጉን የማክበር ፍላጎት እንዲቀንስ አልፎ ተርፎም ወደህገወጥነት እንዲገቡ የሚገፋፋቸው ይሆናል። በተለይም ጉቦ ካልከፈልክ በስተቀር አይወሰንልህም የሚል አመለካከት ካለ ይህ ለፍትህ ስርአቱ በጣም አደገኛ ሁኔታ ነው። ይህ ጥናት በፍትህ አካላት የሙስና ሁኔታ አስፈሪ ሳይሆን ዝቅተኛ እንደሆነ አመልክቷል። ይሁንና በሚዲያዎችም ሆነ በተለያዩ መድረኮች በፍትህ አካላቱ ሙስና የከፋ ደረጃ እንደደረሰ አድርጎ የማየት ሁኔታ አለ። ምንም እንኳን በዚህ ጥናት የተሰባሰበው መረጃ እንዳሳየው ሙስና የመፈጸም ሁኔታው በፍትህ አካላቱ ውስጥ ዝቅተኛ ቢሆንም፣ የህዝቡን አስተያየት በሚመሩት ሚዲያዎች አካባቢ ያለው ሁኔታ በፍትህ አካላቱ ያለውን እንቅስቃሴ ወደአልተፈለገ አቅጣጫ የሚመራው ነው የሚሆነው። ህብረተሰቡ በፍትህ አካላት ላይ የሚኖረው የተሳሳተ ግንዛቤ አንዱ በሚዲያዎች አማካይነት ሆነ ተብሎ ወይም ሳይታሰብበት የሚሰራጨው ትክክለኛ ያልሆነ ዘገባ ነው። እንዲህ አይነት የተዛቡ መረጃዎች እንዳይሰጡ ፍርድ ቤቶች ለሚዲያው ስለፍርድ ሂደቱ መግለጫ የሚሰጡበት አሰራር መዘርጋት፣ ችሎት አዳራሽ ላይ ሚዲያዎች እንዲገኙ ማመቻቸት፣ የተዛባ መረጃ እንዳይሰጥ የራሱን አስተዋጽኦ ያደርጋል። በመጨረሻም የፍትህ አካላት ሀላፊዎች በዚህ ጥናት የተጠቆሙ መፍትሄዎችን ተግባራዊ ማድረግ እና የፍትህ አካላት ስለስራቸው ህብረተሰቡ እንዲያውቀው በራቸውን ክፍት በማድረግ መረጃዎችን መልቀቅ፣ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ እራሳቸው መረጃዎችን ወደሚዲያው እያቀረቡ በህብረተሰቡ ያለውን የአመለካከት መዛባት ለመቀየር መስራት ይጠበቅባቸዋል።